# በርቀት ለሚካሄዱ ችሎቶች (ሪሞት ሂሪንግስ) ለመከታተል የሚያገለግሉ ጠቃሚ ምክሮች- የአከራይና ተከራይ ቅርንጫፍ (ላንድሎርድ ኤንድ ቴናንት ብራንች)

*ፍርድ ቤቶች በኮቪድ-19 ወይም ኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ምክኒያት ዝግ ናቸው። የፍርድ ቤት ችሎትዎ በርቀት ሊካሄድ ይችላል። ይህ ማለት ችሎቱን የሚከታተሉት ወደ ፍርድ ቤት በአካል በመምጣት ሳይሆን በቴሌፎን ወይም በቪድዮ ኮንፈረንስ ይሆናል ማለት ነው። እንዴት መዘጋጀት እንዳለብዎ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።*

### በርቀት የሚካሄድ ችሎት እንዳለኝ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

ችሎትዎ በርቀት የሚካሄድ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ይነግርዎታል። ኢሜይል በመላክ፣ ደብዳቤ በፖስታ በመላክ ወይም በመደወል ሊነግርዎት ይችላሉ።

### በርቀት በሚካሄድ ችሎት እንዴት መሳተፍ እችላለሁ?

በርቀት በሚካሄድ ችሎት እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ደረጃ-በደረጃ የሚያሳዩ መመርያዎች ፍርድ ቤቱ ይሰጥዎታል። በጽሁፍ የተላከልዎ ማስታወቂያ የጠፋብዎ ከሆነ መመርያዎቹ ይሰጥዎት ዘንድ የፍትሐብሔር ክፍል የድጋፍ አገልግሎቶች ዘንድ በሚከተለው ይደውሉ፡ (202) 879-1148

### ችሎቱ ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሜ ማድረግ የሚገባኝ ነገር አለ?

- ቴሌፎን ወይም ኮምፒውተር ስለሌልዎት በችሎቱ መሳተፍ የማይችሉ ከሆነ ወዲያውኑ ፍርድ ቤቱን ያሳውቁ።
- የህግ እርዳታ ለማግኘት ጠበቃ ማናገር ሊያስፈልግዎ ይችላል።

  የአከራይ ተከራይ ሪሶርስ ሰንተር/ የአከራይ ተከራይ አሲስታንስ ኔትወርክ

  202) 780-2575
- በተጨማሪ፣ በ dccourts.gov/coronavirus "ጠበቃ ለሌላቸው የህግ አገልግሎቶች አቅራቢዎች ዝርዝር" በሚለው በመጫን የህግ አገልግሎቶች አቅራቢዎች ዝርዝር ማግኘት ይችላሉ።
- ማስረጃ፡ ፎቶዎች፣ ቪድዮዎች ወይም ሰነዶች መጠቀም የሚፈልጉ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት ዳኛውን ያሳውቁ።
- ምስክሮች፡ ምስክር ምስክርነት እንዲሰጥ የሚፈልጉ ከሆነ በተቻለ ፍጥነት ዳኛውን ያሳውቁ።
- ማመቻቸትና የቋንቋ ተደራሽነት (አኮሞዴሽንስ ኤንድ ላንጉጅ አክሰስ)፡ ለችሎትዎ አስተርጓሚ ወይም ሌላ ማመቻቸት የሚፈልጉ ከሆነ ፍርድ ቤቱን ያሳውቁ።

### ለችሎቱ የሚያገለግሉ ጠቃሚ ምክሮች

- ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብለው ችሎቱን ይቀላቀሉ!
- ኮምፒውተርዎን ወይም ቴሌፎንዎን ይሙሉ (ቻርጅ ያድርጉ)፣ ችሎቱን ለመቀላቀል በቂ ደቂቃዎች እንዳለዎትም እርግጠኛ ይሁኑ። የብቻ (ፕራይቬት) እና ጸጥ ያለ ቦታ ይፈልጉ። የሚቻል ከሆነ ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት ክፍል ውስጥ ብቻዎት ይሁኑ። በሚቻለው መጠን ትኩረትዎ ከሚረብሹ ነገሮች ይቆጠቡ። ክፍሉ ውስጥ ሌሎች ሰዎች ከርስዎ ጋር ካሉ ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት ጸጥ እንዲሉ ይጠይቋቸው።
- እየተናገሩ ካልሆነ ማይክሮፎንዎን ድምጸ-ከል (ሚዩት) ያድርጉ።
- በቴሌፎንዎ ወይም ኮምፒውተርዎ ያሉትን ሁሉም ድምጾች ድምጸ-ከል (ሚዩት) ያድርጉ።
- መዝገቡ ግልጽ ይሆን ዘንድ መናገር ከመጀመርዎ በፊት ስምዎን ይናገሩ። በችሎቱ ያለዎትን ተራ ለይቶ ለማሳወቅ ዝግጁ ይሁኑ (ለምሳሌ፡ ታዛቢ፣ ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ምስክር፣ ወዘተ)።
- እየተናገሩት ያሉትን ተሳታፊዎች በሙሉ ይሰሙት ዘንድ በዝግታና ግልጽነት ባለው አኳሀን ይናገሩ።
- መዘግየት (ላግ) ካጋጠመ ከመናገርዎ በፊት ለአፍታ ያቁሙ (ፖዝ ያድርጉ)። ከቻሉ የጆሮ ማዳመጫ (ሄድሴት ወይም ሄድፎንስ) ይጠቀሙ። እንዲህ ቢያደርጉ እጆችዎንና ድምጽዎን በበለጠ ነጻ እንዲሆኑ ያስችላል።
- ሌላ ሰው እየተናገረ እያለ ላለመናገር ይሞክሩ። በአንድ ጊዜ መናገር የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው። ሌላ ሰው እየተናገረ እያለ ቢናገሩ ዳኛው ሊያዳምጥዎ አይችልም።
- ለችሎቱ የሚጠቀሙባቸው ሁሉንም ሰነዶችዎ ከፊትዎ ያድርጉ።
- ማስታወሻዎች ይወስዱ ዘንድ እስክርቢቶና ወረቀት ይኑርዎት።
- ለችሎትዎ ዝግጁ ካልሆኑ፣ ወይም ጠበቃ ማናገር ቢፈልጉ፣ ችሎቱ ወደ ሌላ ቀን ያራዝምልዎ ዘንድ ዳኛውን መጠየቅ ይችላሉ።
- ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት ድምጽዎ ወይም ቪድዮዎ ቢረጋ (ፍሪዝ ቢሆን)፣ የቴክኒክ ችግሮች እንዳለብዎ ለማሳወቅ የውይይት ባህሪን (ቻት ፊቸር) ይጠቀሙ ወይም የጸሀፊ ቢሮ (ክለርክ'ስ ኦፊስ) ዘንድ ይደውሉ።

### በቪድዮ ለሚካሄዱ ችሎቶች የሚያገለግሉ ልዩ ጠቃሚ ምክሮች (ለተጨማሪ መረጃ እዚህ ይጫኑ)

- ቀደም ብለው የፍርድ ቤቱ የችሎት ሶፍትዌር የሆነውን ዌብኤክስን (WebEx) በማውረድ (ዳውንሎድ በማድረግ) ይሞክሩት! ፍርድ ቤቱ ችሎቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ የዌብኤክስ ሊንክ ይሰጥዎታል።
- ካሜራው በአይንዎ ልክ (አይ ለቨል) ያስተካክሉት። ቴሌፎንዎን እየተጠቀሙ ከሆነ ቴሌፎኑን ሳይይዙ ይመለከቱት ዘንድ አስደግፈው ያስቀምጡት።
- ሲናገሩ ወደ ካሜራው ይመልከቱ፣ በቪዲዮው ከመንቀሳቀስም ይቆጠቡ።
- ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ የሚለብሱት አይነት ልብስ ይልበሱ።
- ከኋላዎ ብሩህ መብራቶች በሌለው በደንብ ብርሃን ባለው ክፍል ውስጥ ይቀመጡ።
- የሚቻል ከሆነ ከፊት ለፊቱ የሚቀመጡበት ባዶ ግድግዳ ይፈልጉ። ዳኛው ሁሉንም በስክሪንዎ የሚኖረው ስለሚመለከቱ ትኩረት የማይረብሽ ቦታ ይምረጡ።